"ጳጉሜን ለኢትዮጵያ"

# የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽን

**አዲስ ዓመት** ለኢትጵያውያን የብሩህ ተስፋ ጅማሮ የተስፋ ስንቅ የምንሰንቅበት ልዩ ስሜትን የሚፈጥርልን ክብረ በአልን በጋራ የምናከብርበት ለየት ያለ መገለጫችን ነው::

እየተገባደደ ባለው 2015 ዓ.ም የህዝባችንን ህይወትና ንብረት ከአደጋ የመከላለልና አደጋም እንዳይደርስ የቅድመ የማስጠንቀቅ **አገልግሎት** በከፍተኛ ትኩረት ተሰርቷል ::

በአገልግሎትም ቢሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች ቢኖሩም ከህዝብ ፍላጎት አንጻር አሁንም ቀሪ የቤት ስራዎች እንዳሉብን ይታመናል::

ስለሆነም በ2015 ዓም ካለፉት ችግሮቻችን በመማርና የነበሩንን ስኬቶቻችንን አጠናክረን የተሻለ ውጤት ላይ ለመድረስ በርትተን በለውጥ ስሜት መትጋት ይጠበቅብናል::

አዲሱን አመት ለመቀበል የሽግግር ጊዜ በወርሀ ጳጉሜ ከስድስቱ ቀናት እንደሚከተለው ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንንቀሳቀሳለን:::

- ጳጉሜ 1 ፤ የአገልጋይነት ቀን
- ጳጉሜ 2 ፤ የመስዋእትነት ቀን
- ጳጉሜ 3 ፤ የበጎነት ቀን
- ጳጉሜ4፤ የአምራችነት ቀን
- ጳጉሜ5፤ የትውልድ ቀን
- ጳጉሜ6፤የአብሮነት ቀን በመባል ይታሰባል::

ማገልገል ከምንም በላይክብር የሆነ ተግባር ነው:፤ ዜጎችን በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በሌሎችም መብቶች ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል ነው ::

የሥራ መርሐ-ግብርንና ፖሊሲን መሠረት በማድረግ እንደተቋም ተደራጅቶ መንቀሳቀስ ነው:: በመደበኛው ወይም በተለመደው አሠራር ሊፈጸሙ ያልቻሉ ጉዳዮችን የተሻለ ማስፈጸምና ለ ውጤት ለማሳየት ጥረት የሚደረግበት ነው:: አገልግሎት ሁሉ ሰው እድሜውን ሁሉ እየሰጠ እና እየተቀበለ የኖረበት የህይወት አካል ነው ::አገልጋይነት በእውነት ለገባው ትንሽ ትልቅ የማይባል ከደሳሳ ቤት ጀምሮ እስከ ቤተመንግስት ያለ የነበረ እና ወደፊትም የሚኖር ታላቅ ተግባር ሲሆን መርሁም ታማኝነት ቅንነት እና አክብሮት ነው:::

ይህ ታላቅ ተግባር አንዱ ማንነታችን ነውና በዚህ ቀን ይወደሳል:: **አገልግሎት የሚሰጠውም ክብር ይሰጠዋል ::**

## በኮሚሽን መስሪያቤታችን የሚሰጡ ዋና ዋና አገልግሎቶች

- የስልጠና አገልግሎት
- የግንዛቤ ማስጨበጫ አገልግሎት
- የሙያ ምክርና ቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ
- የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጥ
- የአደጋ ማስረጃ መስጠት አገልግሎት
- የማረጋጋት አገልግሎት
- የቅድመ ሆስፒታል ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት

## ኮሚሽን መ/ቤቱ ለተገልጋይ የሚገባው ቃል

የአዲስ አበባ ከተማአስተዳደር የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎችን መከላከልና መቆጣጠር በከተማው ውስጥ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ተፅእኖ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በመከላከል የአደጋ ክስተቶችን ለመቀነስ አደጋዎች ሲከሰቱም ፈጥኖ በመድረስና በመቆጣጠር ለከተማዋ ልማት ለህብረተሰቡ ህይወትና ንብረት ደህንነት ተግቶ በመስራት እርካታ አመንጪ አገልግሎት ለመስጠት ቃል ይገባል::

በህብረተሰቡ ህይወትና ንብረት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመቀነስና የአደጋ ደህንነት ስሜት ለመፍጠር የአገልግሎት አሰጣጡን ዘመናዊና ቀልጣፋ በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት በመፍታት የህዝቡን የመገልገያ መብቶች በተመሟላ ሁኔታ ማስጠበቅና የዜጎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ አገልጋይነት በተጠያቂነት ያለበትና ክብር ሚያጎናፅፍ በመሆኑ በከፍተኛ ዝግጁነትና ተነሳሽነት ለመፈም ቃል እንገባለን፡፡ ህዝቡን ማገልገል ድርብ ደስታ ነው፡፡





ለፈጣን የአገልግሎት ዝግጁነት!



## የአገልግሎትቀን! መሪ ቃሎች

- *አገልጋይነት የህሊና እርካታ፤የስብዕና አክሊልነው!*
- *በታማኝነት አገለግላለሁ፤አደራዬን እወጣለሁ!*
- *አገልጋይነት ክብርም፤ታላቅነትምነው!!*
- *ዝቅ ብለን ከአገልግለን፤ታላቅ ሃገር እንገነባለን!*
- *አገልጋይነት እውነተኛ ጀግንነትነው!*
- *ሀገሬን መቼም፣የትም በምንም ሁኔታ አገለግላለሁ!*
- *አገልግሎት በታና ሁኔታ፤አይመርጥም*